+++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

የዕለት እንጀራ

መጋቢት ፴ ፪ ጴጥሮስ ፫፡፲-፲፫ ፳፲፭

የዐቢይ ጾም እያንዳንዱ ሳምንት (እሁድ) ከጌታችንና አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ስራ ጋር በተያያዘ ስም ተሰጥቶት ተከፍሏል:: ይህ ሳምንት ኒቆዲሞስ (ዮሐንስ ፫፡፩-፲፪) ይባላል::

አሁንስ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ። ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ ኢዮ፪፡፲፪-

የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፥ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይቀልጣል፥ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል። ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ፥ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኰላችሁ፥ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይፈታል፤ ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።

አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፥ ቍጣው የዘገየ፥ ምሕረቱም የበዛ፥ ለክፉትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ። ኢዮ ፪፡ ፲፫

በዚህ ዕለት ከሚታሰቡት መካከል፡

ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ፡ ቅዱስ ማርቆስ

እንዲያውቁት	እንዲያውቁት
ሆሳዕና - ሚያዝያ 4 (April 12)	ስቅለት - ሚያዝያ 9 (April 17) ትንሳኤ - ሚያዝያ 11 (April 19)